**የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ)**

***Ethiopian People's Revolutionary Party (EPRP)***

(አንድነት/United)

ሐምሌ ፮ ቀን ፳ ሺህ ፰ ዓ. ም
July 13, 2016

# ከእባብ እንቁላል እርግብ አይጠበቅም!

ህወሓት ገና ከአፈጣጠሩ ጀምሮ በአጥፊነት የተሰማራ ቡድን ነው። እስካሁን በተጓዘበት ዘመን በብዙ ሺህ የሚቆጠር የንፁሃንን ሕይወት ቀጥፏል፤ ብዙ ንብረት አውድሟል። በሚሊዮን የሚቆጠሩ ስዎችን ከሰላማዊ ኑሯቸው አፈናቅሏል። ህወሓት ይህ ከአመሠራረቱ ጀምሮ የተጠናወተው ፀረ-ሕዝብነት ሥልጣን ይዞም ይበልጥ ባስበት እንጂ አልተሻለውም። ኢትዮጵያን በዘር ፈሰስ ሸንሽኖ ሕዝባችን አብሮ እንዳይቆም እያደረገ ያለ አገዛዝ ነው። ብዙ ሰላማዊ ታጋዮችን የተለያዩ ሰበቦችን በመፍጠር በአሰቃቂ እስር ቤት ውስጥ አጉሮ እያሰቃያ ያለ አገዛዝ ነው። በደቡብ ምዕራብ የአገራችን ክፍል ባዶ እጃቸውን ሰላማዊ ሰልፍ የወጡ የዩኒቨርስቲ ተማሪዎችን አፋኝ ኃይሎችን አሰማርቶ በአሰቃቂ ሁኔታ መጨፍጨፉ የትናንት ትዝታችን ነው። በወቅቱ እየታፈሱ ወደ እስር ቤት የተወረወሩ ተማሪዎች እስካሁን ድረስ አልተፈቱም፣ አንዳንዶቹም የት እንደደረሱ አይታወቅም።

ከሁለት ወር በፊት እኛ አማራ እንጂ ትግራይ አይደለንም በማለት በሰላማዊ መንገድ ጥያቄ ያነሱ የወልቃይት/ጠገዴ ተወላጆችን በአሰቃቂ ሁኔታ በዳንሻና በማይ ካድራ ጨፍጭፏል፤ አስሯል። አካባቢውን ለቀው እንዲወጡ የተደረጉ የአካባቢው ተወላጆች ንብረታቸውን ተቀምተው ተባረዋል። ከመኖሪያ ቤታቸውና ከሥራ ቦታቸው ታፍነው የተወሰዱ ወገኖቻችን እስካሁን ድረስ በእስር ላይ ናቸው።

ይህ ደም የጠማው አገዛዝ ዛሬ ደግሞ በሰላም በሚኖረው የጎንደር ሕዝብ ላይ ልዩ አፋኝ ጦር ከትግራይ ክልል በማምጣት ጦርነት መክፈቱን በተለያዩ የዜና አውታሮችና የጎንደር ከተማ ኗሪ ከሆኑ ኢትዮጵያውያን ወገኖቻችን ለማረጋገጥ ችለናል። እስካሁን ድረስም ጦርነቱ እንደቀጠለ ነው።

**P.O.Box 91384**
**Los Angeles, CA 90009**

**Phone: 202- 241 2078**
**eprp_united@eprp-ihapa.com**

የህወሓት አገዛዝ ቃል አቀባይ እንደተናገረው ይህ ልዩ አፋኝ ቡድን ከአገዛዙ መመሪያ ተሰጥቶት ጎንደር የገባ መሆኑን አልሸሸገም። አፋኙ ጦር የመጣበት ምክንያት የወልቃይትን የማንነት ጥያቄ የሚመሩትን የኮሚቴ አባላት አፍኖ ለመውሰድ እንደሆነ የታመነ ነው። ይሁን እንጂ የኮሚቴው አባላትም ሆኑ የመረጣቸው ሕዝብ የአገዛዙን የራሱን ሕገ መንግሥት ጠቅሰው በሰላማዊ መንገድ የመብትና የማንነት ጥያቄ አነሱ እንጂ አገዛዙ እንደሚለው ፀረ-ሰላም ሆነው አይደለም። ከኤርትራ አገዛዝም ጋር ምንም ዓይነት ግንኙነት የላቸውም። ፀረ-ሰላም ቢሆኑ ኖሮ ከተማ ውስጥ በሰላም ባልተቀመጡም ነበር። ሰዎቹን ወደ ፍርድ ቤትም ሆነ ወደ ህግ ለመውሰድ አፋኝ ጦር አስፈላጊም አልነበረም። ዋናው ዓላማ የጎንደርን መሬት በዘላቂነት የህወሓት ንብረት መሆኑን ለማረጋገጥ በሕዝቡ ሥነ-አዕምሮ ላይ ተጽእኖ ለመፍጠር የተደረገ እርምጃ መሆኑ የሚያጠያይቅ አይደለም።

በጎንደርና በተለያዩ ቦታዎች የተከሰቱት ሁኔታዎች ህወሓት ተደላድሎ ሕዝቡን መግዛት ከማይችልበት ደረጃ መድረሱን ነው። ስለሆነም ሕዝባችን ለመብቱ የሚያደርገውን ትግል ጠንክሮ እንዲቀጥል ኢ.ሕ.አ.ፓ (አንድነት) ጥሪውን እያስተላለፈ ከጎኑ የቆመ መሆኑንም ያረጋግጣል። ኢ.ሕ.አ.ፓ (አንድነት)

- ከመኖሪያቸው ታፍነው የተወሰዱ ሁሉ ያለ ምንም ቅድመ ሁኔታ እንዲለቀቁ በጥብቅ ይጠይቃል።
- በውጊያው ምክንያት ቤተሰባውን ላጡ ወገኖቻችን መጽናናቱን እንዲሰጥልን ይመኛል።
- ዛሬ የጎንደር ታጋዮችን ከቤታቸው አውጥቶ የወሰደ አገዛዝ ነገ በሁሉም የኢትዮጵያ ክፍል የሚደግመው በመሆኑ በየተራ እየተነሳህ መደብደብ ይብቃህ፣ እጅ ለእጅ ተያይዘህ ህወሓትን ለአንዴና ለሁልጊዜ ከትከሻህ ላይ አሽቀንጥረህ ለመጣል ተባብረህ ታገል ይላል።
- ለኢትዮጵያ ሕዝብ የዴሞክራሲ መብት የምንታገል ድርጅቶች ሁሉ በአንድነት በመቆም ጠንካራ ኅብረት እንፍጠር ይላል።

የንፁሃን ደም በከንቱ ፈሶ እንዳይቀር በኅብረት እንታገል!

P.O.Box 91384
Los Angeles, CA 90009

Phone: 202- 241 2078
eprp_united@eprp-ihapa.com